**የመንፈስን አንድነት መጠበቅ፣ ኤፌ 4፡1-16፣ መዝ 133፡1-3፤)**

ከኤፌ 4፡1- 6፤ ያለው የመጀመሪያው ጥቅስ የተጠራንበት ጥሪ እንዳለና ለዚያ ጥሪ የተገባ ኑሮ እንድንኖር ይናገራል፡፡የተጠራነው ለምንድነው? ወደ ክርስቶስ ወንጌል (ለእግዚአብሔር መንግስት የምስራች ቃል፣) ወደ ክብሩና፣ ወደ ዘላለም ሕይወት ተስፋ ነው፡፡ ፊሊጵ 1፡27፣ 1ተሰ 2፡12፣ ኤፌ 4፡4፤

ስለዚህ በዚህ ጌታ ኢየሱስ እጅግ ታላቅ ዋጋ በከፈለበት እኛ ግን የምስራቹን ቃል እውነተኛነት በማመን ብቻ ድነትን የሚያህል ታላቅ ስጦታ በነጻ የተቀበልን ቢሆንም አኗኗራችን ግን ይህንኑ የሚመጥን መሆን እንዳለበት በማስረዳት የመንፈስ አንድነት እንድንጠብቅ ይጠይቃል፡፡

**ትርጉም፡-** የመንፈስ አንድነት መጠበቅ ማለት በክርስቶስ ያገኘነው መንፈሳዊ ተዛምዶ በማያቋርጥ እንክብካቤ በመያዝ፣ ወደ ጋራ ተስፋችን የዘላለም ሕይወት መውረስ ጋ ለመድረስ እንደ አንድ ሰው ሆኖ መስራት ማለት ነው፡፡ (በየሰበብ አስባቡ ከመለያየት ጌታ ኢየሱስ እያንዳንዳችንን ከነ ጉድለታችን እንደ ተሸከመን እኛም መሸካከም ያሻናል፤)

የመንፈስ አንድነት አማኙ ሕዝብ የሚፈጥረው፣ (የሚመሰርተው) ሳይሆን በአባላቱ ጭራሽ ሳይታሰብ እግዚአብሔር የመሰረተውና በክርስቶስ ኢየሱስ የሰራው ሥራ ውጤት ነው፡፡ አንድነቱ እንደ ስጋ ዘር አንድነት/ጊዜያዊና የሚጠፋ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ የሆነና ለዘላለም የሚቀጥል አንድነት ነው፡፡

በክርስቶስ ያመኑትን አንድ ያደረገው (አንድነቱ የተገኘው) በምንድነው፡- ኤፌ 4፡3-6

1. **በአንድ አካል፡-** ገላ 3፡28፣ ቆላ 3፡11፣ አንድ አካል በተለያየ ትውልድ ዘመን፣ ከመላው ዓለም የተለያዩ አገራት፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና ከተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው የዳኑት ሁሉ ስብስብ የሚያካትት ነው፡፡ 1ቆሮ 12፡13
2. **በአንድ መንፈስ፡** - ከጌታችን ጋር በሞቱና መቀበሩ ለመተባበር በውሃ ሲጠመቁ ወዲያውኑ በአንድ መንፈስ ቅዱስ፣ አንድ ጥምቀት ተጠምቀዋል፡፡ 1ቆሮ 12፡13፣ "አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፣ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል፡፡" ኤፌ1፡13፣ 2፡18፣ 22፣ 3፡ 16፣ 4፡3፤
3. **በአንድ ተስፋ፡-** ቲቶ 1፡2፤ 3፡7 የተባረከ ተስፋችን የሆነው የታላቁ አምላካችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር መገለጥና በእርሱ የዘላለም ሕይወት የመውረስ ተስፋ ነው፡፡ ኤፌ 1፡18፣ 1ዮሐ 2፡24-25፤
4. **በአንድ ጌታ፡-** ስለሁላችን ኃጢአት ሕይወቱን መስዋእት አድርጎ በሕይወቱ ዋጋ የተቤዠን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ስናምን አዲስ መንፈስ ተሰጥቶን መንፈስ ከሆነው ጌታ ኢየሱስ ጋር አንድ አካል ክፍሎች ሆነናል፤

ከዚህ መንፈሳዊ አካል መለየት አንድ የሰውነት አካል ብልት ተነጥሎ እንደ መውጣት ያህል ነው፡፡ ሮሜ 12፡5፣ "እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፡፡ እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን፡፡"
ገላ 3፡28፣ "በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፣ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ፡፡"
1ቆሮ 12፡12፣ "አካል ብዙ ብልቶች ቢኖሩትም አንድ አካል ነው፤ ነገር ግን ብልቶች ብዙ ቢሆኑም አካል አንድ ነው፡፡ ክርስቶስም እንደዚሁ ነው፡፡" ይላል፤ በዓለም ሁሉ ላይ የነበሩ ያሉና ወደፊትም በጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ እስከሚመጣ ድረስ በጌታ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የአንዱ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት አካል ክፍሎች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

5. **በአንድ እምነት**፡- ዮሐ 14፡6፣ "መንገዱ እኔ ነኝ፣ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡" ሐሥ 4፡12 "ድነት በሌላ በማንም የለም፣ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም የለም፡፡"
   እንደሚለው ቃሉ በእውነት መዳን የሚያስችል አንድ እምነት በጌታ በኢየሱስና ባስተማረው ትምህርት ማመን ብቻ ስለሆነ እምነታችን አንድ አድርጎናል፡፡ ሐዋሪያቱ ያስተማሩት ከእርሱና ከመንፈስ ቅዱስ የተማሩትን ነው፡፡ ዮሐ 1፡1-4፣ 10፣12-14፤ 3፡15-16፤
6. **በአንድ ጥምቀት**፡- ሮሜ 6፡3-5፣ 8፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ካመኑ በኋላ በውሃ ጥምቀት የሚጠመቁት ቀድሞ ያደርጉት የነበረው ኃጢአት ላለማድረግ በመወሰን ሞቶ የተቀበረ ሰው ኃጢአት ማድረግ እንደማይችል ሁሉ ከእንግዲህ ወዲያ ኋጢአት እንደ ማያደርጉ መወሰንን ለማመልከት ነው፡፡ የውሃ ጥምቀት የሚወስዱት አንድ ጊዜ ብቻ እንጂ የሚደጋገም አይደለም፡፡

7. **በአንድ አምላክ እግዚአብሔር አብ**፡ - ከሁሉም በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሰራ፣ በሁሉም የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አባታችን ስለሆነን፡፡ ኤፌ 4፡6

በእግዚአብሔር በኩል ተሰርቶ ያለቀለት አንድነታችን ይህን ሲመስል፣ በሌላ በኩል ኤፌ 4፡11-13፣ ወደፊት የምንደርስበት አንድነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህም ማለት እኛ በክርስትና ትምህርት፣ በእምነትና ጌታን በማወቅ እያደግን ክርስቶስ ኢየሱስን እየመሰልን ስንሄድ አንድነታችን ይበልጥ እየጠነከረ የሚሄድ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ይበልጥ ጌታን ባወቀነውና ራሳችንን ለቃሉ ባስገዛን ልክ የመንፈስ አንድነታችን የጠበቀ ወይም ልል ሊያደርገው ይችላል፡፡

በሰዎች መካከል ለመከፋፈል ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ቢጠቀሱም ዋነኛ ምክንያቱ ሰይጣንና ከክፉ ምኞት የሚወለድ ኃጢአት ነው፡፡ ያዕ 4፡1፣3፡፡ ኃጢአት ሁልጊዜ ይከፋፍላል፣ ያጣላል፣ ጠብ ያመጣል/ያዋጋል፡፡ የሚለያየውም/የሚያጣላውም ሰውና

አምላኩን፣ ሰውና ሰውን የጌታ በሆኑት መካከል ሳይቀር፣ ከዚያም አልፎ በአንድ ሰው ውስጥ እንኳ ነፍስና መንፈሱ በማያቋርጥ ውጊያ ውስጥ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ለመለያየት ሌላው አስተዋጽኦ የሚያደርገው የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ዕውነት በበቂ ሁኔታ የመረዳት ጉድለት ነው፡፡

የክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ስራ የሚያተኩረው ኃጢአት በመለያየት ህብረቱን አበላሽቶት የነበረው በማፍረስ ቀድም በኃጢአት ምክንያት መውደቅ ከመታየቱ በፊት ወደ ነበረው ስምምነትና ኅብረት ለመመለስ ነው፡፡

እግዚአብሔርም ይኸን ስለሚያውቅ የሥጋ ዘር አንድነት ጠብቁ ባይልም ሁሉም የሰው ዘር እንደ ራሳችን እንድንወድ አዞናል፡ አድሎአዊነትን እንድናስወግድ ይፈልጋል፡፡ ሌዋ 19፡ 33፡34፤ ሚልክ 2፡10፤ ማቴ 12፡30፣ 31፤ ሮሜ 2፡11

ኅብረቱ በእግዚአብሔር የተሰራና በጸጋው ለሰው የተሰጠ ሲሆን የሰው ድርሻ መቀበልና ማስቀጠል ነው፡፡

## አንድ የሆኑት እነማን ናቸው?

ሀ. ያመኑት ከእግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ጋር፤ ማቴ 28፡19፣ 20፤

ለ. በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ እርስበርሳቸው

## የአንድነቱ ምስረታ/ጅማሬ ሂደት ቅደም ተከተል

ሀ. እያንዳንዱ አማኝ ከላይ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት በመመስረት ተጀመረ፣ 1ዮሐ1፡3፤ እያንዳንዱ ሰው ጌታን በእምነት ለመቀበል ሲጀምር በአብዛኛው ከሌሎች በክርስቶስ ከሚየምኑት ጋር ኅብረት ለመፍጠር በማሰብ አይደለም፡፡ አዳዲስ አማኞችም እያደር ሕብረት ለመፍጠር አጀንዳ ይዘው ተሰባስበው በመነጋገር ስምምነት ላይ በመድረስ ሳይሆን ሳያስቡት ከላይ በተጠቀሱት ሰባት ኃይሎች አንድ ተደርገው ነው የሚያገኙት፡፡

ሲበላሽ ግን ብዙውን ጊዜ ቀድሞ ከላይ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ሳይሆን ከታች በአማኙ ሕዝብ መካከል ባለመስማማትና በመቃቃር ይጀምራል፡፡ ሁኔታው ከቀጠለ ከእግዚአብሔርም ጋር ወደ መለያየት ሊያደርስ ይችላል፡፡ ስለዚህ ቀድሞ መስተካከል ያለበትም ከታች ይሆናል፡፡ የጎንዮሽ ኅብረት ተበላሽቶ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት ጤነኛ አድርጎ ለረጅም ጊዜ ማስቀጠል በተለይም ለጥፋተኛው ወገን አይቻልም፤

1 ዮሐ 3፥15፣ "ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ታውቃላችሁ።" ይላልና፤ ማቴ 5፡ 23-26፤

አንዳንዴ በእግዚአብሔር ያለ እምነት ሲደክም ህብረቱ ከላይ ጀምሮ ሊበላሽ ይችላል፡፡

ለ. ከዚያ ተከትሎ የጎንዮሽ (አማኞች) ህብረት ተገኘ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ስንሆን ብቻ ነው እርስ በርሳችን እውነተኛ መንፈሳዊ ህብረት ሊኖረን

የሚችለው፡፡ የአንድነታችን ግንዱና መሰረቱ አግዚአብሔር አብ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ነው፡፡ ዮሐ 15፡5፤ ሮሜ 12፡5፤ 1ቆሮ 1፡10፤

**ይህ አንድነት ምን ዓይነት አንድነት ነው?**

የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ የሆኑት በመንፈሱ የተጠመቁት/ህብረት ያገኙት፣ የክርስቶስ ኢየሱስ አካል ክፍሎች የሆኑት፣ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያድርባቸው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነት አንድነት ነው፡፡

በወንጌሉ ቃል እውነት አስተምህሮ በአንድ ልብና አሳብ/አቋም፣ ራዕይና ተልዕኮ በመያዝ ለአንድ ግብ ማለትም እርስ በርስ እየተጋገዙ በክርስትና ህይወት/በመልካም ፍሬ በማደግ ሌሎች ወደ ክርስቶስ መንግስት እንዲጨመሩ መስራትና አዎንታዊ የህይወት ተጽእኖ ለማሳደር/በመልካም አኗኗር አርአያ መሆን ነው፡፡ ፊሊጵ 2፡2

**ይህን አንድነት ለማጠናከርና ለማስቀጠል በጋራ ሊኖሩት የሚገባ ኑሮ (የሚከናወኑ አንኳር ተግባራት)**

**ሀ.** ሁሉም በተሰጠው ጸጋ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ እንዲያድጉና ጌታ ያዘጋጀላቸውን ክብር ለመውረስ እንዲበቁ በመስራት አንዱ ጌታችንና አምላካችንን ማገልገል ነው፡፡ ኤፌ 4፡7፣ (ማስተማር የሚችለው ተግቶ በማስተማር፣ ሌላው በመማር)

**ለ.** ቃሉን በጋራና በግልም እያጠኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውና ያልሆነው በመለየት፣ በቃሉ እውቀትና እምነት ማደግ፡፡ ይሄ ከሌለ አንዱ የሚናገረው/የሚያደርገው ነገር ለሌላው ጆሮ ባዕድ ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡ ማቴ 22፡29፤

**ሐ.** ቅድስናን ዓላማ አድርጎ በመነሳት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ከእግዚአብሔር የተማሩትን ቃል ተግባር ላይ ማዋል፤ ቆላ 3፡5-14፣

**መ.** በጋራ ተሰባስቦና በተናጠልም አንዱ ስለራሱና ስለሌላው መጸለይ፣ እግዚአብሔርን በጋራና በግል ማመስገንና ማወደስ፡፡ ቆላ 2፡1-3፣ ያዕ 5፡13-15-16፤

**ሠ.** በወንጌል ምስክርነት በጌታ ኢየሱስ ያላመኑትን ለመድረስ በሚከናወነው ሥራ በተለያየ መንገድ በሁሉም የጋራ ተሳታፊነት መስራት፤ እንዲሁም፡-

- እርስ በርስ በሰላም በሚያስተሳስረው የወንድማማች ፍቅር መዋደድ ቆላ፣ 3፡14፣ ዮሐ 13፡34፣ ሮሜ 13፡10፤
- እርስ በርስ ይቅር በመባባል፤ ቆላ 3፡13፣ 1ጴጥ 3፡9 አፌ 4፡2፣ አግዚአብሔር ፍቅርና ህብረት ባለበት ይኖራል/ይሰራል፡፡ ማር 11፡25-26፤ በፍቅር ተቻቻሉ፣ ታገሱ ኤፌ 4፡2፣

- በየጊዜው ተሰባስበው እየተነጋገሩና እየተመካከሩ ፈጥኖ ለመታረም መዘጋጀት፤ መታረም ያለባቸው ነገሮች በጊዜ ማስወገድ/መበረታታት፤ መከፋፈል የሚፈጥሩ ነገሮችን ሳይከፋፍሉ በፊት አስቀድሞ እልባት መስጠት፣ ዕብ 10፡23-25፣

በየጊዜው መሰባሰብ ያስፈለገበት ተጨማሪ ምክንያት በክርስቶስ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ስለሆንን ከመፈቃቀር የተነሳ መነፋፈቅ ስላለ፣ እርስ በርስ ያለንን ነገር ስጦታ/ችሎታ ለመከፋፈል (አብሮ ለመብላት፤ ለመማማር፤ ለመጽናናት፤ ለመጸለይ፤ መደጋገፍ በምንችለው ሁሉ በመደጋገፍ የእምነት ጉዞዋችንን ከፍጻሜ ለማድረስ)፡፡ ሐሥ 2፡44-45፣ 4፡32-34፣ ሮሜ 14፡19፣

- ቅሬታ ሲፈጠር እውነትን በፍቅርና በአክብሮት በሚያንጽ ቃል በመናገር፣ በገርነት ማቅናት፣ ኤፌ 4፡15-16፣29-30፣
- እያንዳንዱ ለራሱና ለሌላውም ጥቅም የሚሆነውን እንጂ ለግሉ ብቻ የሚጠቅመውን አለማድርግ፤ (እንደ አንድ አካል መሆን፤) ፊጵ 2፡4፣ ቆላ 3፡15፣
- ፍጹም ትሁታንና ገሮች መሆን፣ ኤፌ 4፡2፣ እርስ በርስ እግር መተጣጠብ፣ (እንዳችሁ ለሌላችሁ እንደ አገልጋይ ሁኑ)፣ ዮሐ 13፡14፣ ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ ቁጠሩ፤ ፊሊጵ 2፡3-4፣ ሮሜ 12፡10፣ 1ጴጥ 5፡6፣
- በመስማማት መኖር፣ ዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ካሉት ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ፣ ሮሜ 12፡16፤ … አንዱ በሌላው ላይ ከመፍረድ ይቆጠብ ሮሜ፣ 14፡13፤ 19፣
- በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፣ ኤፌ 4፡3፣ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ዕብ 12፡14 ሮሜ 12፡18፣

የተጠየቅነው አንድነትን ፍጠሩ ሳይሆን በእግዚአብሔር የተሰራውን አንድነት ጠብቁ ነው፡፡

አንድነት እንዳለን ሁሉ ልዩነትም አለን፡፡ የተለያየ የአገልግሎት ስጦታዎች አሉን፡፡ እያንዳንዳችን የራሳችን የአገልግሎት ስጦታ ትኩረት እንዲሰጠው መፈለግ ሊኖር ይችላል፡፡ ዋናው ተግዳሮት ግን ከስጋ ስራ የመላቀቃችን ደረጃ መለያየቱ ነው፡፡ እኔ በአገልግሎትና በጽድቅ ህይወት ስተጋ ሌላው ለምን አይተጋም ማለትና ሰውን ማየት ይከሰታል፤ ዛሬ የእግዚአብሔር ቤት ስራ ለግል ፍላጎት፣ ጥቅም ለማዋል መስራትና የመሳሰሉ ችግሮች የሚታዩበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ መገፋፋት ሊታይ ይችላል፡፡ ያም ሆኖ እያለ የእግዚአብሔር ቃል የመንፈስን አንድነትን ጠብቁ ይላል፡፡ ስለዚህ ባሉት አንዳንድ ችግሮች ላይ ማትኮር ትቶ፡-

- ራስን ወይም ሌላ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ብቻ ደስ ለማሰኘት መስራት፤ የተሰጡት የአገልግሎት ሃላፊነት ካለ ከእግዚብሔር ወሮታ ለመቀበል እንደሚሰራ ሰው

መስራት፡፡ ዮሐ 14፡15፣ 21፣ 23፣ ሰው ለእግዚአብሔር በመገዛት ህይወት መኖሩ በዋናነት የሚጠቅመው ለራሱ ነውና፤

- መሳ 3፡1-2፣ እንደ ስጋ ፈቃድ የሚመላሱት የሚያሳዩት አካሄድ በጽድቅ ሕይወት ራስን ለማሰልጠን እንደ መለማመጃ እንደተሰጠን ወስዶ የጽድቅ ምላሽ በመስጠት፤ የማይመች ተግባር የሚፈጽሙ አማኞች ፊት መልካም ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራት በመፈጸምና በማቅናት ለመስራት ራስን ማዘጋጀት ነው፡፡ በጌታ የሆኑትን መታገስና ፍቅር ማሳየት ከቻሉ በውጭ ባሉት ፊትም ብርሃን መሆን ያስችልና ወደ ጌታ ይሳባሉ፡፡ ማቴ 5፡14 እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ ይላልና፤

- የሰውን ጉድፍ ማየት ቶቶ የራስን ጉድፍ አጣርቶ በማየት ማስወገድ፡፡ ማየት ያለብን ጌታ ኢየሱስን ምሳሌነት ነው፡፡ ማቴ 7፡3

- የሰው ድክመት መከታተል ትቶ ጥንካሬውን በማየት ማትኮር፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ብዙ መልካም ነገሮች አሉት፤ እነዚያ ጥንካሬዎች በመለየት ለተገቢ ስራ መጠቀም ከቻሉ እያደር ደካማ ጎኑን እያስተካከለ ይሄዳል፤ ሉቃ 6፡37፣ ያዕ 4፡12፣

- በተለያየ መንገድ ሰውን መውደድ የሚየስችለው ነገር ለእርሱ መልካም እንዲሆን በመጸለይ መትጋት ነው፡፡ ሉቃ 6፡28 "የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚበድሏችሁም ጸልዩ፡፡"
- የአንዱን ሸክም ለማቅለል መረዳዳት/መተጋገዝ (አገልግሎት…፤) ገላ 6፡2
- ሰውን ሁሉ ማክበ፣ር 1ጴጥ 2፡17፤
- እርስ በርስ መተሳሰብ፤ በአንድ አሳብ መስማማት፤ 1ጴጥ 3፡8፣
- ለመሪዎችና አንዱ ለሌላው መገዛት፣ ኤፌ 5፡21
- እርስ በርስ መቀባበል- ሮሜ 15፡7፣ (በእምነት የደከመውን፡- በቅድስና ህይወት፣ በእግዚአብሔር ቃልና ኃይል ታላቅነት እውቀት ደከም ያለውን) እንግዳን/የተቸገረን መቀበል/መርዳት፤ ሮሜ 14፡1-3፤15፣
- እርስ በርሳችን መበረታታት፣ ሮሜ 1፡12፣ ዕብ 10፡25
- እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ ፣1ተሰ 4፡18፣ 5፡11፣ …ተሳሰቡ 1ጴጥ 3፡8፣
- እርስ በርሳችሁ መለያየት እንዳይኖር ተስማሙ፣1ቆሮ 1፡10፣ ማር 9፡50፣ ገላ 5፡15
- እርስ በርሳችሁ በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ፣ 2ቆሮ13፡12፣

… ቸሮችና ሩህሩሆች ሁኑ፣ ኤፌ 4፡32፣ 1ተሰ 5፡15፣ ለሌሎችም መልካም አድርጉ

… አትወቃቀሱ፣ ቆላ 3፡9፤ አታጉረምርሙ፣ ዮሐ 6፡43፣ ፣ አትወነጃጀሉ፣ ያዕ 4፡11፣

… ተማማሩ፣ ተመካከሩ/ተወያዩ ቆላ 3፡16፣ ኀጢአት ተናዘዙ፣ ያዕ 5፡16

ተመርጦ የሚተው ነገር ሳይኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁሉ ማድረግ እንደሚገባ ኢየሱስ ምሳሌ ሆኖልናል፡፡ በንግርና በአቀራራብ ብቻ የሚገለጽ ውጫዊ ትህትና ሳይሆን ከውስጥ የሚመነጭ ትህትና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር ራስን በመስጠት ከውስጥ የሚጀምር ነው፡፡ ትህትና የሚገለጠው በመገዛት ነው፡፡ የራስን ፈቃድ ትቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ፡፡ የእግዚአብሔርን ቁጣ በመፍራት ብቻ ሳይሆን ለፍቅሩ የፍቅር ምላሽ በመስጠት ነው፡፡ የመጨረሻ የሚናቅና አነስተኛ ተደርጎ የሚቆጠረውን ስራ ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ መፈጸምም ያጠቃልላል፡፡ በሰዎች ለመናቅ ዝቅ ተደርጎ ለመታየት ፈቃደኛ መሆን ነው፡፡ ትህትና የምናሳየው በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ሳይሆን ለሹማምንት /ለባለስልጣናት/፣ ለቤተክርስቲያን መሪዎች፣ በእድሜ ለሚበልጡ ሰዎች፣ ሁሉም ሰው ለሌላው ሰው ሊያሰየው የተገባ ነው፡፡ 1ጴጥ 2፡13፣ 5፡5

ትህትና መጀመር ያለበት በመንፈስ ድሃ ከመሆን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ንጹህና ፍጹም አድርጎ የሚያቀርበኝ ከራሴ የሆነ የጽድቅ ስራ የሌለኝ ድሃ ነኝ በማለት በአእምሮው የተቀበለ፡፡ ማቴ 5፡3 በቀድሞ አኗኗሩ/ድርጊቱ የሚያፍር ነው፡፡ ጳውሎስ እንዳለው ከኃጢአተኞች ዋነኛ እኔ ነኝ የሚል 1ጢሞ 1፡15፡፡ የቀድሞም ሆነ የአሁን ጥቂት መልካም ስራ አለን የምንለው ነገር ቢኖር እንኳ ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር ሲስተያይ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ የተራራቀ መሆኑን የተገነዘበ፣ ስለዚህ የራሱን ጽድቅ እንደጉድፍ የሚቆጥር ነው፡፡ ፊሊጵ 3፡3-9፣ ኢሳ 64፡6፣ ሉቃ 7፡1-7፡፡

ትህትና የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ፣ በእግዚአብሔር መንግስት ታላቅ መሆንን ያስገኛል፣ በጸጋ ላይ ጸጋም ያስጨምራል፡፡ ማቴ 5፡3፣ ሉቃ 7፡28 ያዕ 4፡10

ከኤፌ 4፡11-16፣ ያለው ክፍል እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑትና ወደፊትም የሚያምኑት ሊደርሱበት ያቀደላቸው ልክ ምን እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ለዚህም ተግባር የተለያየ መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸው የመንግሥቱ ሰራተኞች በየትውልዱ በስሙ ከተጠሩት ሕዝብ መካከል ለይቶ በመምረጥ አስነስቶ እየሰጠ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በእነዚህ ሰራተኞቹ አማካይነት የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ-ክርስቲያን እየተገነባችና ቅዱሳንም ለአገለልግሎት ሥራ የማዘጋጀቱ ሂደት እንዲቀጥል ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ በስሙ የተጠራው ሕዝብ በየትውልዱ በሚከሰተው የሐሰት ትምህርት ነፋስ እንዳይወሰድና በሰው ሰራሽ ማታለያ ዘዴዎች እንደ ሕጻናት በመሳብ ወደ ጥፋት እንዳያመራ ለመጠበቅ ነው፡፡

ይህም ተግባር በየትውልዱ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ከሕጻንነት ተላቀው ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከሚደርሱ ነው። ኤፌ 4፥13

ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)   2019 ዓ.ም.